ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

*የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ*
*ነሐሴ 25 ቀን 2007 ዓ.ም. የተላለፈ*

## <u>የመሥዋዕት ጠቦት ፍለጋ</u>

ለመሥዋዕትነት ተዘጋጅቶ መሥዋዕት ለመክፈል መወሰንና የመሥዋዕት ጠቦት ፍለጋ የተለያዩ ናቸው። የመጀመሪያው በዕምነት ላይ ከተመሰረተ ውሳኔ ላይ በመድረስ፤ የህይወት ዋጋ እስከመክፈል የሚያደርስ ቁራጥና የመጨረሻ ርምጃ መውሰድ እንደሚሆን ይታመናል።ይህንን ውሳኔ ለመውሰድ የማንንም አስገዳጅ ኃይልና ግፊት የሚጠይቅ አይደለም። መሥዋዕቱን ለመቀበል ከተዘጋጀው ግለሰብ የሚወሰድ የግል ውሳኔ ነው። መሥዋዕት፤ ሊተኩ ከሚችሉ ጥቃቅን ነገሮችና ቁሳቁሶች ጀምሮ፤ የሕይወት ዋጋ እስከመክፈል ድረስ ያለውን ሁሉ ያካትታል። የጊዜ፤ የጤና፤ የሀብት -ንብረት- የቤተስብ፤ የሀገርና የወገን ፍቅር የመሳሰሉትን ሁሉ እስከመክፈል ድረስ የሚያስገድድም ይሆናል ። ሁሉም፤ እንደ አቅሙ እንደ መጠኑ፤ ችሎታውና ፈቃዱ ይከፍላል ። መሥዋዕቱን ሲከፍልም፤ ፀፀትና ቁጭት አይስማውም። በአንፃሩ ግን፤ መሥዋዕት በመክፈሉ ዘለዓለማዊ ደስታ ይሰማዋል ። ውለታም ሆነ ክፍያ አይጠይቅም ። የሠማዕታቱን ክብር አውቆ ወሮታ የማይከፍል ኅብረተሰብ ግን ፣ ራሱን አዋርዶ ውለታ- ቢስ ሆኖ ይቀራል ።

" ይብላኝ ለናንተ እንጅ ጓዛችን ቀላል ነው ፤ ከፈን ግዙ አንልም ፤ ሳጥን አንጠይቅም፤

ለአፅማችን ማረፊያ ቦታ አናጣብብም፤ ተስካር አውጡ አንልም ፤

ለታሪክ መፃፊያ ብርዕ አናስቀርፅም ፤ ቀለም አናስገዛም ።

ቀለሙ ደማችን፤ ብርዑ አፅማችን መሆኑን አውቀናል ፤

ዕዳችን ተወጥተን፤ ታሪካችን ጽፈን በኩራት አልፈናል ።

ሐውልት አያሻነም ፤ ውለታ አንጠይቅም ፤ ሕዝብ አናስቸግርም ፤

ጥንትም ስንሰዋ፤ ለነፃነት እንጅ፤ ለውዳሴ ከንቱ፤ ለዝና አልነበረም ። "

ብለው የጀግና ህልፈት አሳልፈዋል ።

ጫጩት ለጭልፊት፤ ቅጠል ለፍየል፤ ፍየሏ ለነብር፤ ሳሩ ለበጓ፤ በጊቱ ለተኩላ ፤ አህያዋ ለጅብ፤ ጊደሯ ለአንበሳ፤ ይበላሉ። ይገደላሉ። ይጠፋሉ ። ወደውም ሆነ ተግድደው፤ መሥዋዕት ይሆናሉ። የተበዮቹ መበላት፤ ለበይዎቹ መኖር ይጠቅማል ። የአንዱ ሞቱ ለሌላው ህይውቱ ይሆናል ። ከሳርና ስንበሌጥ የተሰራው ሰበጥራ እንኳን ሳይቀር፤ ከሳት በተጣደው ምጣድ ላይ ያለውን ዕንጀራ ለማውጣት በግድ የጋለውን እሳት ቃጠሎ መቅመስ አለበት። ሰበጥራው ተቃጥሎ ያወጣውን እንጀራ ሰው ይበላዋል ። በዚህ ምክንያት ግዑዙ ስበጥራ፤ እንደ ሰው አፍ አውጥቶ ፤ ዕሮሮውን ያሰማል።

" አየ እኔ ሰበጥራ፤ የሰው እንጀራ አውጭ ተቃጠልኩ ለሌላ ፤

በእሳት ተንገብግቤ ፤ የአዳም ልጅ ሊበላ ። "

አለ ይባላል።

ሁለተኛው፤ የመሥዋዕት ጠቦት ፍለጋ የሚደረገ ጥረት ነው። የራስን ድክመትና ጥፋት፤ ወንጀልና ሃጢአት ለመሸፈን ሲፈለግ፤ በግድ የመሥዋዕት ጠቦት ፈልጎ ለዕርድ የማቅረብ ተንኮል ነው። በዚህ የመሰሪነት ተንኮል የተካኑ ክፍሎች ፤ የንጹሃንን ታሪክና ስብዕና ከማበላሸት ጀምሮ፤ በሚጠሉት ሰው ላይ የገፀ ባኅርይ ግድያ (character Assassination ) እስከመፈፀም ደረስ ከመሄድ አይመለሱም ። የራሳቸውን ዓላማ ሊያሳካላቸው ይችላል ብለው እስካመኑበትም ድረስ፤ የሚጠሉትን ሰው ወደ ቁስ አካልነት ለመለወጥ የማያደርጉት ጥረት የለም ። ዞሮ ዞሮ ፤ የዚህ ሁሉ ድካም፤ የመከላከያ ምሽጋቸውን ለማጠንከርና የመሥዋዕት ጠቦት በማቅረብ፤ ራሳቸውን ከደሙ ንፁህ ነን ለማለት ነው። ከሚያስጠይቀው ኃላፊነት ለመሸሽም ጭምር ነው።

በዚህም ሆነ በዚያ፤ ሰለባ የሚሆኑት፤ ለተለያየ ምክንያትና ዓላማ የመሥዋዕት ጠቦት ሆነው የሚቀርቡት ንፁሃኑ ናቸው። በታሪክ፤ ብዙሃን የዋሆች፤ አርቆ-አስተዋዮች፤ ጀግኖች፤ አርበኞች፤ የሃይማኖት ሰዎች፤ ሊቃውንትና ጠቢባን፤ ፃድቃን፤ ሰማዕታትና፤ ሐዋርያት የመሥዋዕት ጠቦት ሆነዋል። ለዕምነታቸው፤ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው፤ ለዓላማቸውና ለቃል-ኪዳናቸው፤ ለመርኅና ለአቋማቸው ሲሉ የመሥዋዕት ጠቦት እየሆኑ አልፈዋል ። ይህ ክስተት፤ ፍትኅ-ርትዕ በሌለበት ህብረተሰብ ውስጥ፤ ለመሥዋዕት የተዘጋጁ ዐርበኞች እስካሉ ድረስ ይቀጥላል።

በኃይል ረግጬ ልግዛህ የሚል ኃይል በአንድ በኩል፤ አሻፈረኝ አልገዛም ብሎ የሚያምፅ ኃይል በሌላ በኩል ሆነው ተፋጥጠው በሚኖሩበት ሀገር፤ የመሥዋዕት ጠቦት ማግኘት አይቸግርም። በዳይና ተበዳይ፤ ጨቋኝና ተጨቋኝ፤ በሚኖሩባትም ኢትዮጵያ፤ ለመሥዋዕት ጠቦት የሚቀርቡ ዜጎች አይጠፉም !

በታሪካችን ሂደት ውስጥ፤ የመሥዋዕት ጠቦት ሆነው ታሪክ ያስመዘገቡት አያሌ ሰማዕታት ነበሩ። የሁሉንም ስም ለመዘርዘር ከአቅም በላይ ይሆናል። ለአብነት ሲባል ግን፤ የጥቂቶችን ማንነት ብቻ ጠቅሶ ማለፉ በቂ ነው ብለን እንገምታለን ።

ታዲያ፤ የሁሉንም ሰማዕታት ስም ሊወክሉ ይችላሉ በሚል ተስፋ፤ በጣም ጥቂቶቹን ፤ በክብር እናወሳለን ። እናስታውሳለን ። የአኩሪ ታሪካችን አካል ስለሆኑም ፤ እያከበርን እናመሰግናቸዋለን ! ተተኪው ትውልድም ባለውለታቸው እየሆነ ይቀጥላል ። የነገዋ ኢትዮጵያም እያበበች በነፃነቷ ትኖራለች ! አኩሪ ታሪኳም በቀጣይነት ይቀጥላል ። አጥፊዎቿም መቀመቅ ይወርዳሉ !

የእንግሊዝ ኮሎኒያሊስቶችን ጥቃት ለመቋቋም የተሰለፈውን ዳግማዊ ቴዎድሮስ፤ ካህናቱና ባላባቱ ሰለከዱትና አንዳንዶቹም ከባዕዳኑ ጋር ስለተባበሩ፤ መቅደላ ላይ የመሥዋዕት ጠቦት አደረጉት። ወለል ፊታውራሪ ዓለማየሁ ጎሹ፤ በወቅቱ በነበረው የፖሊቲካ አመራር ድክመት ምክንያት፤ ለኢጣሊያን ወራሪ ኃይል አጋዴን ጠርፍ ላይ፤ የመሥዋዕት ጠቦት ተደርጎ ደሙ በረሃ በልቶት ቀርቷል። ሁለቱ ጀነራሎች፤ ተፈሪ ባንቲና አማን አምዶም፤ የቅርብ ጊዜዎቹ የመሥዋዕት ጠቦቶች ናቸው። ከዚያም፤ ዕልፍ አዕላፍ የሕዝብ ተቆርቋሪዎች የመሥዋዕት ጠቦት ሆነው የትም ቀርተዋል ። ዛሬ፤ ታሪክን በቀድዶ- ጥገና (Doctor) ለውጥ የሚደረገው መፍጨርጨር፤ የሰማዕታቱን

ጀግንነትና አንፀባራቂ ኮከብ ሊያደበዝዘው አይችልም ። ለጊዜው የተዳፈነ ቢመስልም ፤ ነገ የዕውነት ብርሃን ይፈነጥቅለታል ።

" እናት አልረገመኝ፤ አባት አልረገመኝ ፤

መሥዋዕት መከፈሉ ፤ ዘንድሮም ደገመኝ ። "

የሚል እንጉርጉሮ በማብዛቷ ምክንያት ይሁን አይሁን ባይታወቅም ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ፤ በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች፤ ሀቀኛ ልጆቿ የመሥዋዕት ጠቦት እየሆኑ ያልቁባታል ። እርሷም በበኩሏ፤ ልክ እንደ አራስ ነብር ሆና ልጆቿን ከአጥቂ ጠላቶች መከላከል ሲገባት፤ ጭራሹን፤ እንደ ድመት የራሷን ልጆች ራሷ እየበላች ቆይታለች። ይህ ክስተት ደግሞ በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል ። ይህ ጥቃት አንድ ቦታ መቆም አለበት! ማን እንደሚያቆመው፤ ሁሉም ዜጋ ሊያስብበት ይገባል ። እኛ ግን ማሳሰባችንን እንቀጥልበታለን !

ከፋሽስት ጣሊያን 1928 ዓ.ም. ወረራ በፊት ጀምሮ፤ በግንባር ቀደም ፤ ለኢትዮጵያ የተፋጠነ ዕድገትና መሻሻል ታጋዮች መካከል አንዱ ብላታ ታከለ ወልደ ሐዋርያት ነበሩ። ሳይሰለቹና ሳይታክቱ፤ በሥልጣንና በጥቅም ሳይደለሉ፤ በተቃውሞ ኖረዋል ። በመጨረሻ፤ ከንጉሡ የፀጥታ ኃይሎች ጋር ሲታኮሱ ሕይወታቸውን አሳልፈዋል ። ሌሎችም ስመ-ጥር ዐርበኞችና የመሻሻል ለውጥ ፈላጊ ሀገር ወዳድ ምሁራን ፤ እንደ ቢትወደድ ነገሽ በዛብህ ፤ አለቃ ፈጠነ ፤ መምህር ዮሐንስ ረማህ፤ መቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስ፤ ሰዐሊ አገኘሁ ዕንግዳ፤ ጀኔራል መንግሥቱ ነዋይ፤ አቶ ገርማሜ ነዋይ ፤ አቶ ገርማሜ ወንዳፍራሽ ፤ ኮ/ል ወርቅነህ ገበየሁ ፤ ፊታውራሪ ኃይሉ ክብረትና ሌሎቹም የመሥዋዕት ጠቦት እየሆኑ አልቀዋል ። የእነኝህን ግንባር ቀደም ሠማዕታት ታሪክ መስታወስ፤ የዜግነት ግዴታና የትግላችንም ኃላፊነት እንደሆነ ይሰማናል ። ይህንን ለማለት የሚያስችለን መሰረታዊ ምርኩዝ አለንም ብለን እናምናለን።

ይኸውም፤ ማንነታችን የተሟላ ሊሆን የሚችለው፤ ያለፈውን ታሪካችንን አስታውሰን ስናከብር እና ዛሬ ያለንበትን ሁኔታ ተገንዝበን ፤ መፃኢ- ዕድላችንን ለመቀየስ የሚያስችለንን ከኅሎት እናገኝበታለን ብለን ስለምናምን ነው ። በታሪካችን ላይ የተመሠረተ ማንነት ተመርኩዘን የምናካሂደው ትግል ፤ በመጨረሻ አቸናፊ እንደሚሆን ጥርጣሬ አይኖርም። ማነናታችንን ማክበር የምንችለው ደግሞ ፤ ለታሪካችን ቀናዒ መሆናችንን ስናረጋግጥ ነው። ታሪክ ያለው ሕዝብ፤ ለታሪክ ያለው ግንዛቤ የለቀ በመሆኑ፤ ማንነቱን የሚዳፈሩትን ሁሉ ያለመታከት ይዋጋቸዋል ። ወያኔዎች ይህንን ባለመረዳታቸው፤ ከማይወጡት አዘቅት ውስጥ ገብተዋል ። አሳፋሪ ታሪክ ያላቸው ስለሆኑ፤ የኢትዮጵያን አኩሪ ታሪክ እንዲያከብሩ አይጠበቅባቸውም ።

በ 1933 ዓ.ም. እና በ1966 ዓ.ም. መካከል የተፈጠረውም ትውልድ በበኩሉ፤ ለሀገሩና ለሕዝቡ ፍቅር ብሎ ፤ ለህይወቱ ሳይሳሳ፤ የመሥዋዕት ጠቦት ሆኖ አልፏል ። ማንም ሰብዓዊ ፍጡር፤ ለሚወድደው ሁሉ፤ ፍቅሩን ለመግለፅ የሚችለው፤ የመጨረሻ ክፍያ ህይወትን አሳልፎ በመስጠት ነው። ይህንን ከፍተኛ ዋጋ የከፈለው፤ በዚህ በተጠቀሰው የዘመን ክልል የነበረው ቆራጥ ኢትዮጵያዊ ትውልድ መሆኑን ማንም አሌ ሊለው አይችልም። ይህ አሳረኛ ትውልድ፤ የመሥዋዕት ጠቦት እየሆነ አልፏል ። መሥዋዕትነቱ ዋጋ ቢስ ሆኖ ቀርቷል ባይባልም፤ የመሥዋዕቱ ዋጋ ግን የተፈለገውን ውጤት አላስመዘገበም ። ዓላማውም ግቡን ገና አልመታም ። ግቡን እስኪመታ ድረስ፤ የማይቀረው መሥዋዕት መከፈሉ ግን አይቀርም ።

አሁን ሀገሪቱ ካለችበት ተጨባጭ ሁኔታ መረዳት እንደሚቻለው፤ ኢትዮጵያ ሀገራችን፤ ዛሬ የኅልውናዋ ጥያቄ በመስቀለኛ መንገድ ላይ በመሆኑ፤ አሁንም እንደ ትላንቱ ብዙ መሥዋዕት ሊሆኑ የተዘጋጁ ጀግኖች እንደሚያስፈልጓት ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ግልፅ እየሆነ መጥቷል ። ይህ ክሰተት አንድ ቦታ መቆም አለበት ከተባለ፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሀገራችን መሠረት እንዲጥል የግድ ነው ። የፍትኅ-ርትዕ መስፈን፤ ቅድመ-ሁኔታ አይኖረውም ።

መሥዋዕት በመከፈል አዙሪት እየተሽገረገሩ መኖር አስቸጋሪ መሆኑ ባያከራክርም፤ መሥዋዕት የመክፈሉ አስገዳጅ ምክንያቶች እስካልቆሙ ድረስ፤ የመሥዋዕት ጠቦት እየሆኑ ከማለፍ በስተቀር ሌላ አማራጭ ሊኖር አይችልም ። ይህንን ለማለት፤ የሚቻለው በሚከተሉት እንቅልፍ ነሽ ምክንያቶች ነው ።

1ኛ. ለኢትዮጵያ ጥቅም የቆመ መንግሥት አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን፤ በተፃራሪው ሀገሪቱን በስልት እያጠፋና ሕዝቧንም እየበታተነ ያለ ከይሲ ብሄረተኛ ቡድን ባስቸኳይ መወገድ ያለበት በመሆኑ ነው። እርሱን ለማስወገድ ደግሞ፤ ከፍተኛ መሥዋዕት የሚጠይቅ ትግል አስፈላጊና ዋሳኝ መሆኑ ለጥያቄ የሚቀርብ አልሆነም ። ሊሆንም አይችልም ።

2ኛ. እስካሁን፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ የጓጎለ ደም እጃቸውን የታጠቡ ክፍሎች አሁንም እንደገና የንጹሃንን ደም ለማፋሰስ የሚያደርጉትን ትብበር ባጭሩ መቅጨት ያስፈልጋል ። የትሮጃን ፈረስ ለመሆን የሚያቆበቁቡት ሁሉ እንደገና ሊያስቡበት ይገበል።

" ተው በሉት ያንን ቂል መካር የለውም ወይ፤

ምላጭ ከተሳበማ/ አረር አይደለም ወይ ? "

ተብሎ ሊነገራቸው ያስፈልጋል። በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ እየገቡ ችግር የሚፈጥሩ ሁሉ፤ የኋላ ኋላ ማጣፊያው እንደሚቸግራቸው አናውቃለን ። ኢትዮጵያ፤ ወድቆ መነሳት፤ ተጠቅቶ ማጥቃት፤ ተነጥቆ መቀማት፤ አጥቶ ማግኘት፤ ተበትኖ መዋሃድ ታውቅበታለች ። ትችልበታለችም !

3ኛ. እንደ ጥንቱ - እንደ ጧቱ፤ ብሎም፤ እንደ አባት አደሩ፤ ኢትዮጵያውያን/ያት ራሳቸው የመሥዋዕት ጠቦት በመሆን፤ ሀገራቸውን ነፃ ማደረግ ሲችሉና ሲገባቸው፤ ሀገራቸውን ያፈረሰ ከይሲ ቡድን፤ ይተባበራል ብሎ መሞኘት፤ ባልተገባ ነበር።

4ኛ. የወሎ፤ የጎንደርና የጎጃም ሕዝብ እንደገና ለሦስተኛ ጊዜ፤ ለሌሎች ሥልጣን መዋጣጫ እንዲሆን ሊፈረድበት አይገባም ። የደርግና የወያኔ ግፍና በደል ይበቀዋል ። ለሻአቢያና ለወያኔ፤ መደራደሪያና የመሥዋዕት ጠቦት ሊሆን አይችልም ። ከእንግዲህ ወዲያ !

5ኛ. የውጭ ባዕዳንም ሆኑ ሻዓቢያና ወያኔ የቅድሚያ " ጠላታችን " የዐማራው ሕዝብ ነው " ብለው ስለወሰኑ፤ "ነብርን ሲወጉ በፍየል ይጠጉ " በመሆኑ፤ አማራውን ለማጥፋት ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በእርስ ለማፋጀት

እንደታቀደ ይቆጠራል ። " ያልጠረጠረ ይመነጠራል ! " የተባለውን ብሂል ደግሞ ደጋግሞ ማስታወስ ጠቃሚነቱ ከዚሁ ላይ ነውና።

6ኛ. በወያኔ የጥፋት ዘመቻ ምክንያት፤ የአማራው ብሄር እየተመነጠረ በመጥፍት ላይ ነው። ይህ የማጥፋት ዘመቻ በቶሎ ካልተገታ፤ ዝርያቸው በአደጋ ላይ እንደሚገኘው እንሥሣትና አዝርዕት ( Endanger Species ) እየሆነ መሄዱ የማይቀር ነው።ይህ እንዳይደርስ ከተፈለገ፤ የዐማራው ሕዝብ፤ ለሁለት ነገሮች ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል።

ሀ. መጀመሪያ እራሱን ከጥፋት ማዳን አለበት ። እስካሁን እንደታየው ማንም ሊደርስለት አልቻለምና !

ለ. እራሱን ከአጥፊዎቹ እየተከላከለ፤ ሀገሩ ኢትዮጵያ ጨርሳ ከመውደሟ በፊት፤ በግንባር ቀደም፤ የመሥዋዕት ጠቦት በመሆን ኢትዮጵያን ማዳን የጠበቅበታል ። " እኔ ከሌለሁ ኢትዮጵያ አትኖርም የሚለውና ኢትዮጵያ ከሌለች እኔ ልኖር አልችልም " የተበለው አቋም አንድ አካል አንድ አምሳል ናቸው ተብሎ ስለሚታመን፤ ያንዱ መጥፋት የሌላውም ጥፋት እንደሆነ ሊቆጠር ይገባል ።

7ኛ. ዛሬም እንደወትሮው፤ ለመሥዋዕት የተዘጋጀ ቆርጦ የተነሳ አዲስ ትውልድ ሀገሪቱ በማፍራት ላይ ትገኛለች ። አዛውንቱ እያለፉ መሥዋዕት ከፋይ አዳዲስ ትውልድ መተካቱ የተፈጥሮ ህግ በመሆኑ፤ የኢትዮጵያ ትንሣዔ ሩቅ አይሆንም ። ወያኔና ሻአቢያም እንደቀለዱ አይቀሩም ።

8ኛ. የሁለቱ ጣምራ ጠላቶች የሰሞኑ አስመሳይ ቅርበት/ (Coalition / ግጭት/ Contention ) ትጥቅ ለማስፈታት የተወጠነ ቲያትር መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው። የእነርሱን ጥቃት እያከሸፉ፤ ኢትዮጵያን ለማዳን የሚደረገውን ትግል ማጠንከር ለዓላማችን ግብ መምታት ወሳኝ ነው ። የአንድነት ኃይሉን ሰርስሮ በመግባት ለመከፋፈል የሚደረገውን ተንኮል፤ ሁሉም በያለበት ነቅቶ መጠበቅና ማክሸፍ አለበት ! የአንድነት ኃይሉ እየተጠናከረ መምጣት፤ የኢትዮጵያን ጠላቶች እያስበረገጋቸው በመሄድ ላይ ስለሆነ፤ ሰላዮቻቸውን፤ አዳዲስ መመሪያ እየሰጡ በማሰማራት ላይ እንዳሉ ተደርሶበታል። በመሆኑም፤ የአንድነት ኃይሉና ሀገር- ወዳድ ዜጋ ሁሉ ፤ " ምሥጢሩን በጉያው፤ ስንቁን በአህያው " እያደረገ የጠላቱን ሴራ ማክሸፍ አለበት ። ዝክርክነት፤ ቸልተኝነት፤ ዳተኝነትና ግብዝነት በአንድነት ኃይሉ ጎራ ቦታ ሊሰጣቸው አይገባም ። ሀገራችን ፤ እስከዛሬ ድረስ፤ ጠላቶቿ ሰርስረው በመግባት ብዙ ጉዳትና ጥቃት አድርሰውባታል ። በአደባባይ ጠርሙስ እያሰበሩ አካኪ ዘራፍ ማለት፤ የግብዞች ፖለቲካ እንጅ፤ የብልሆች አሰራር ዘዴ አይደለም ።

9ኛ ገበናውን በአደባባይ የሚያሰጣ በሙብዛቱ ምክንያት፤ ወያኔዎቹ የስለላ መዋቅራቸውን በቀላሉ ለመዘርጋትና የሚጠቅማቸውን ዜና ለማግኘት አመቺ ሁናቴ ተፈጥሮላቸዋል። የስለላው መሪዎችና ያሰማሯቸው ሰዎች፤ ኢትዮጵያዊ ስሜት ሲያልፍም አይነካቸው። ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ፤ የሚጠቀምበት ዘዴና የበቀል ጭካኔ፤ የናዚ ጀርመኑን ጌስታፖ " ምስጋን ይንሳው " የሚያሰኘው ነው። የወያኔ መሰሪ መሪዎች ፤ ማንነታቸውንና የሚሰሩትንም በሚገባ ያውቃሉ የሚለው እሳቤ ከዕውነት የራቀ ነው ለማለት ባይቻልም ፤ ሌላው ወገን ስለ እነርሱ ሊያውቅ የሚገባውን ሁሉ አውቆ ደርሶበታል ብሎ በዕርግጠኝነት የሚናገር ስንቱ እንደሚሆን ግን ማወቅ ቀላል አይደለም ማለት ይቻላል ። በሌላ በኩል ደግሞ፤ ሙልጭልጩን አሣ ለመጨበጥ ጊዜ ከማጥፋት ይልቅ፤

አሣውን ለማጥፋት ባኅሩን ማድረቅ ይቀላል ነው የሚሉም ተመልካቾች አሉ። በሁሉም እና በሆነውም መንገድ ወያኔን ማጥፋት፤ የወቅቱ አንገብጋቢ ተግባር ሆኗል ።

10ኛ. ወያኔዎቹ፤ ይዘግይም ይፍጠንም፤ መውደቃቸውን ማንም ሳይነግራቸው እራሳቸው ያውቁታል። ከተወገዱ በኋላ ለሚመጣውና ለሚገጥማቸው ለማነኛውም ሁኔታ አስቀድመው እንደሚዘጋጁ፤ አለመከታተል እንዝህላልነት ይሆናል። ከሻእቢያዎቹም ጋር ወደፊት ስለሚኖራቸው የተሃድሶ ግንኙነት ከአሁኑ ተግተው እንደሚሰሩ ማወቅ፤ በኋላ ጉድ ተሰራን ብሎ ከመጮኽ ያድናል። ብልህ ነኝ የሚል ትውልድ በአንድ የታሪክ ዘመኑ ፤ ሁለት ጊዜ ሊታለል አይገባውም ።

ሁለቱም የኢትዮጵያ ጣምራ ጠላቶች፤ ጥንድ ዓላማቸውን በጋራ ለማሳካት፤ ተግተው እንደሚሰሩ መጠርጠር ይኖርብናል ። " ውሾቹ ይጮኻሉ ግመሎቹም ይሄዳሉ " በማለት ብቻ ሳይገቱ ፤ "ተኝተው ሲያንኮራፉ፤ አሁንም ጥለናቸው ሄድን " ለማለት የሚያበቃቸውን ሁኔታ ከመፍጠር ወደ ኋላ አይሉም። የወደፊቱን ዋስትና ለማረጋገጥ የሚችሉት፤ ደካማዋን ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ሆና እንዳትቀጥል በማድረግ ነው። ለዚህም የሚከተሉትን አስተማማኝ ሥራ ይሰራሉ ።+

1ኛ. በበርካታ ሽህ የሚቆጠሩ የኤርትራ ተማሪዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ልዩ ልዩ ዩኒቨርስቲዎችና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ገብተው ይማራሉ። በኢትዮጵያ ደሃ ገበሬ ሀብት !

2ኛ. በተለያዩ የኢትዮጵያ ስትራተጅክ ቦታዎችና ከተሞች ውስጥ ተመድበው በድብቅ፤ የሻእብያ የመረጃ ሰራተኞች የስለላ ተግባር ያከናውናሉ። ከወያኔ መረጃ ጋር የጣምራ ተግባር ያከናውናሉ። የኢትዮጵያን ውስጠ-ምሥጢር ይቦረቡራሉ። ሁለ-ገብ መረጃዎችን ይሳበስባሉ። ይህ ሁሉ ተግባር፤ ለጊዜው ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱ ጥቅሜታቸውም ሲባል ነው።

3ኛ. ዛሬም እንደ ትላንቱ፤ " ከሞኝ በረፍ ፤ ብልሆቹ ሞፈር እየቆረጡ ናቸው:: "

የኛ ተግባር ተጨባጭ ሁኔታውን እየገመገምን ለወደፊት አቅጣጫ ሰጭ ይሆናል ብለን የምንጠረጥረውን ለሕዝባችን ማሳወቅ ካልሆነ በቀር፤ " እኔማ አስቀድሜ ተናግሬ ነበር፤ የሚሰማኝ አጥቼ ነው እንጅ ለሚል ግብዝነት አይደለም ።

4ኛ. ጠላቶቻችንም ይኸንን በሚገባ እንደሚያውቁት እናውቃለን ። ማን ማን እንደሆንን እንተዋወቃለን ። ይኸም ሁኔታ " በአጥፊና- ጠፊ" ደርጃ እንድንሆን አድርጎናል። ከማንም ጋር ቢሆን የጠላትን ስሜት ባይኖርንም፤ በሀገራችን ስትራተጂያዊ ጥቅም ከመጣ ግን የማንንም ወዳጅነት አንሻም። ጠላትነቱም አያስጨንቀንም ። እንዲያውም በበለጠ የመዣዋዕት ጠቦት ለመሆን ብቃት ይኖረናል ።

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ !**

ወዳጅ ጠላትህን እየለየህ፤ አንድነትክን አጠንክር !

አገርህን ለማዳን ተባበር !

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም መኖሯን ትቀጥላለች !